# አድዋ የነጻነት ድል

ለእትዮጵያዉያንና ለእትዮጵያ ወዳጆች በሙሉ የአደዋ ድል የ116ኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል አብረን እንደናከብር በሙኒክ የእትዮጵያዉያን የመረዳጃ ማኅበረ ጥሪዉን ያቀርባል።



ዉድ የተከበራችሁ ኢትዮጵያዉያንና እንግዶቻችን የካቲት 23/1888 አድዋ ላይ የዛሬ 115 ዓመት በአፄ ምኒሊክ II የተመራዉ ጀግናዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ሰራዊት በዘመናዊ መሳሪያ እሰከ አፍንጫዉ የታጠቀዉን ወራሪ የኢጣሊያን ሐይል በጋሻ፣ በጦርና በጎራዴ አንበርክኮ ድልን የተጎናጸፈበት እለት ነዉ:: ይህ እለት ለእኛ ለኢትዮጵያዉያን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ፀረ ኮሎኒያል ትግል ያበረከተዉ አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ በአፈሪካ የነጻነት ታሪክ ታላቅ ስፍራ አለዉ:: ይህንን አስመልክቶ የተከበሩ አቶ ይልማ ኃ/ሚካኤል በጀርመን ራዲዮ የአማርኛዉ ዝግጅት ጋዜጠኛ በክብር እንግድነት ተገኝተዉ ለአዲሱ ትዉልድ መልእክት ያስተላልፋሉ::

የአድዋ ድል የአንድ ክልል ድል አይደለም፣ የአድዋ ድል የአንድ ብሄር ድል አይደለም፣ የአድዋ ድል የአንድ እምነት ተከታይ ሕዝብ ድልም አይደለም የአድዋ ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ነዉ:: በመሆኑም ይህንን ታላቅ የድልና የነጻነት ቀን የጾታ፣ የሀይማኖትና የዘር ልዩነት ሳይለያየን በጋራ እንድናከብር የመረዳጃ ማኅበራችን ወገናዊ ጥሪዉን ያቀርባል::

በአገርህ፣በሕዝብህና በወላጆችህ ጉያ ታሪክህ፣ ባህልህና ወግህ እየተተረከልህ የማደግ እድሉን አጥተህ የራስህን ሳታዉቅ የሌላዉን ለማወቅና ለመማር የተዳረክ ወጣቱ ትዉልድ ሆይ የአገርክንና የሕዝብህን ታሪክ፣ ባህልና ወግ አዉቀህ ለባእዳን እንዲሁም ወደፊት ለልጆችህ የማስተላለፉ ሃለፊነት ስላለብህ በበዓሉ ላይ እንድትገኝና በማኅበራችን እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንድትሆን በዚህ አጋጣሚ ልዩ ጥሪ እናቀርባለን:: ወላጆችም ልጆቻችሁ የነገዋን ኢትዮጵያ የሚረከቡት የትናንቱንና የዛሬዉን ሲያዉቁ መሆኑን በመገንዘብ ይዛችሁ በመምጣት ወይንም እንዲሳተፉ በማድረግ ወላጃዊ ጊዴታችሁን ትወጡ ዘንድ ማስገንዘብ እንወዳለን::

ኢትዮጵያ በልጆቿ ተጋድሎ በነጻነት ለዘለአለም ትኑር

ማሳሰቢያ

- ቦታ Ganghofer str. 41
- ቀን March 03.03.2012
- ሰዐት ከ $14^{00}$ ጀምሮ

በ U5 ከፊለፊት ተሳፍረዉ ወደ Laimerplatz አቅጣጫ እሰከ Schwantalerhöhe ተጉዘዉ በመዉረድ ወደ ግራ ታጥፈዉ 3ቱን ትልልቅ ሕንጻዎችን እንዳለፉ የዝግጅቱን ቦታ ያገኙታል::